## በትምህርት ሚኒስቴር

## ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ

## የ2011 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ነጥብ አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

በ2010 የትምህርት ዘመን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ብቃት መመዘኛ ከግንቦት 27-30/2010 ባለው ጊዜ 281,994 (154,010 ወንዶች፣ 127,984 ሴቶች) መፈተናቸው ይታወሳል።

ከእነዚህ መካከል በመንግሥትም ሆነ በግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በ2011 የትምህርት ዘመን በመደበኛም ሆነ  መደበኛ ባልሆነ የትምህርት ዘርፍ ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ በዘመኑ 295 እና ከዚያ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ትምህርታቸውን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው እንዲከታተሉ ተወስኗል ። በመሆኑም በ2011 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 213,621 ተመዝግበው ትምህርታቸውን መከታተል እንደሚችሉ የሚገመት ሲሆን ይህም በ2010 የትምህርት ዘመን ከተፈተኑት መካከል 75.75% ይሆናሉ።

ከእነዚህም በ2011 ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በመደበኛ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት እንዲማሩ የተወሰነላቸው ተማሪዎች ቁጥር 149,823 ሲሆኑ ከነዚህም መካከል 98,567 የተፈጥሮ ሣይንስ ተማሪዎች 51,256 የሕብረተሰብ ሣይንስ ተማሪዎች ይሆናሉ።

በዘንድሮው የትምህርት ዘመን  የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲማሩ ሲወሰን ታሳቢ የተደረጉ:-

- በ2010 የትምህርት ዘመን ከተወሰኑ ቦታዎች በስተቀር በተረጋጋና የተሻለ የፈተና አስተዳደር የነበረ መሆኑ፣
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን አቅም እያደገ መምጣትና የመማር ማስተማር ሂደት አድጎ መታየቱ፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ አማካይነት በሚደረግ ድጋፍ ተጫባጭ ውጤቶች መመዝገባቸው፣
- በአገሪቱ የመንግሥትና የግል ዩንቨርስቲዎች ቁጥር ማደግ (በግል 134 የግል ዩኒቨርስቲዎችን እና የመንግሥት 11 ተጨማሪ አዳዲስ ዩነቨርስቲዎች መገንባታቸው)፣

ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ National Educational Assessment and Examinations Agency

- በ GTP II እና በ ESDP V የከፍተኛ የትምህርት ዘርፍ የተያዘ ዕቅድና የ2011 የትምህርት ዘመን የተያዘ የግብ መነሻ መሠረት በማድረግ፤
- በከፍተኛ የትምህርት ዘርፍ የትምህርትን ፍትሓዊነትን ለማረጋገጥ
  - የሴቶችን ተሳትፎ ምጥጥን ለማሳደግ፣
  - የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የመማር ተሳትፎ ለማረጋገጥ፣
  - የታዳጊ ክልሎችና የአርብቶ አደር አካባቢ ተወላጅ ተማሪዎች የመማር ዕድል ለማስፋት፣
- በ2010 የትምህርት ዘመን በፀጥታ ችግር ምክንያት በፈተና ወቅት ጫና የነበረባቸውን ትምህርት ቤቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የዘንድሮው የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ተወስኗል።

በዚህም መሠረት

በመደበኛ የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት የ2011 መግቢያ መሥፈርት እንደሚከተለው ይሆናል።

| ተ/ቁ | የተማሪው ዓይነት | ተፈጥሮ ሳይንስ | | ሕብረተሰብ ሳይንስ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| 1 | መደበኛና የማታ ተማሪዎች | ≥ 362 | ≥ 345 | ≥ 345 | ≥ 335 |
| 2 | የታዳጊ ክልል ተማሪዎች | ≥ 345 | ≥ 330 | ≥ 335 | ≥ 320 |
| | አርብቶ አደር አካባቢ ተወላጆች ተማሪዎች | | | | |
| | በፀጥታ ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው ተማሪዎች | | | | |
| 3 | የግል ተፈታኞች | ≥ 375 | ≥ 370 | ≥ 375 | ≥ 370 |
| 4 | መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች | ≥ 275 | ≥ 265 | ≥ 275 | ≥ 265 |
| 5 | ዐይነስውራን ተማሪዎች | - | - | ≥ 210 | ≥ 200 |

በዚህ መቁረጫ ነጥብ አማካኝነት፡-

- 98,567 የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ሲሆኑ 58,233 ወንዶች 40,334 ሴቶች ይሆናሉ፤
- 51,256 የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ሲሆኑ ከነዚህም መካከል 27,625 ወንዶች 23,631 ደግሞ ሴቶች ናቸው፤
- በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውድድር ይገባሉ፤ ተብሎ የሚገመተው 149,823 ሲሆኑ ይኸውም 57.31% ወንዶች 42.69% ሴቶች ናቸው፤
- በትምህርት ዘመኑ በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም 63,790 ተማሪዎች ይሳተፋሉ ተብሎ ይገመታል፤
- በሁለቱም የትምህርት ዘርፍ ማለትም በተፈጥሮ ሳይንስና በማህበራዊ ሳይንስ የተማሪዎች ምጥጥን (Ratio) 65.79% እና 34.21% ሲሆን የዩኒቨርስቲዎች የተማሪዎች የትምህርት ዘርፍ ምደባም ይህንን ምጥጥን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፤
- በተደረገው የአወንታዊ ድጋፍ
    - 177 (118 ወንዶች እና 59 ሴቶች) አይነስውራን ተማሪዎች፤
    - 15 (13 ወንዶች እና 2 ሴቶች) መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች፤
    - 319 (231 ወንዶች እና 88 ሴቶች) የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶአደር አካባቢ ተወላጅ ተማሪዎች፤
    - 1515 (1,036 ወንዶች እና 479 ሴቶች) የታዳጊ ክልል ተማሪዎች

ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በትምህርት ሚኒስቴር

የሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ

መስከረም 3 2011 ዓ.ም